# የጎንደር ደብረ ኀይል ወደብረ ጥበበ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት

## የቤተክርስቲያን ታሪክ ኮርስ




አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ሰኔ ፲፪፣ ፳፻፲፫ ዓ፣ም

## ታሪክ ምንድን ነው?

ሰዎች ሠርተውት ያለፉትና ያከናወኑት ነገር እንዲሁም በቀደመው ዘመን የተፈጸመ ክንዋኔ ሁሉ ታሪክ ይባላል። ታሪክ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ወይም የሰው ልጅ ከአካባቢው ጋር ለዘመናት የነበረውን የትግል ጉዞ አጉልቶ የሚያሳይ የሕብረተሰብእ ሳይንስ ክፍል ነው። ታሪክ ሦስት ዘመናትን ማለትም ትላንትን፣ ዛሬንና ነገን የሚያገናኝ የድርጊትና የጊዜ ሰንሰለት ነው። ታሪክ በመረጃ የተደገፈና ሳይንሳዊ የጥናት ዘዴን ተከትሎ የሚጻፍ እውነታ (Fact) ስለሆነ ከአፈ ታሪክ (Legend) ይለያል።

## የታሪክ ጥቅም

፩. ነገሮችን ከሥር መሠረቱና ከተለያየ አቅጣጫ የማየትና የማስተዋል ልምድን እንድናዳብርና አንድን ነገር በጭፍን ከመቀበል ይልቅ ምክንያታዊ (Logical) ለመሆን።

፪. የትላንት ውሏችንን በመመርመር ዛሬን በጥበብ ለመኖርና ለነገውም በቂ ዝግጅት ለማድረግ ይጠቅመናል።

፫. ማንነታችንንና ምንነታችንን ለማወቅ ይጠቅማል።

፬. ያለፉ ስሕተቶችን ለማረም፣ መልካም ጅምሮችን ለመከተልና ለመፈጸም ብሎም የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ይጠቅማል።

፭. አካባቢን ለመረዳትና ለመጠቀም ይረዳል።

## የታሪክ ምንጮች

- ሰነዶች (Archives)
- ቅሪት አካሎች (Fossils)
- ሳንቲሞች (Coins)
- ጌጣጌጦች (Ornaments)
- የብራና ጽሑፎች (Parchments)
- የድንጋይ ላይ ጽሑፎች (Inscriptions)
- ቤተ መቅደሶች (Temples)
- አብያተ መንግሥታት (Palaces)
- ትውፊታዊ መረጃዎች (Traditional Sources)

ቅርስ የአንድን ሕዝብ የዘመናት የኑሮ እንቅስቃሴ የሥራና የፈጠራ ክንውን የሚያሳይ በመሆኑ ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች መጠበቅ ያስፈልጋል። ቅርሶች የማንነታችን መገለጫዎችና የታሪካችን የመረጃ ምንጮች በመሆናቸው በርካታ ማሕበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ባህላዊ ጠቀሜታ ስላላቸው ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል።

## ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ምእመናን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የተባሉት በአንጾኪያ ሲሆን የመጀመሪያዋ ሕንፃ ቤተክርስቲያን የተሠራችው ደግሞ በፊልጵስዩስ ነው። ቤተክርስቲያን፡-

- ✓ ቤተክርስቲያን ዘክርስቶስ (ሮሜ 16፥16)
- ✓ ቤተክርስቲያን ዘእግዚአብሔር (1ኛ ቆሮ.1፥2)
- ✓ ማኅደረ እግዚአብሔር (ኤፌ.2፥20-22)
- ✓ የጸጋው ግምጃ ቤት (ዕብ.4፥16)
- ✓ የጸሎት ቤት (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1)

እየተባለች ትጠራለች፡፡ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ትርጉም አለው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩. ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን (የክርስቲያኖች ቤት)

፪. እያንዳንዱ ምእመን (የክርስቶስ ወገን) 1ኛ ቆሮ.3፥16-17

፫. የክርስቲያኖች ሕብረት ወይም አንድነት ማቴ.18፥15-17

ሕንፃ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት፣ ስለበደላቸው ምሕረትን ለመለመን፣ ሕይወት የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ለመስማት፣ የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል የሚሰበሰቡባት ናት፡፡ ቤተክርስቲያን የሰማያውያንና የምድራውያን፣ በአካለ ሥጋና በአካለ ነፍስ ግዕዛን ያላቸው ፍጥረታት አንድነት ስትሆን ራሷ ወይም ግንዷ ደግሞ ክርስቶስ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊት ዓለም ናት፡፡

## የቤተክርስቲያን ባሕርይ

- ○ አንዲት ናት (ኤፌ.4፥4-6)
- ○ ቅድስት ናት (1ኛ ጴጥ.1፥15-16)
- ○ ኵላዊት ሕብረታዊት ናት (ኤፌ.1፥23)
- ○ ሐዋርያዊት ናት (ኤፌ.2፥20-22)

አንዲት ናት ስንል በወርቅ በነሐስ፣ በጨፈቃ በጭቃ ብትሠራም ክብሯ አንድ ነው ማለታችን ነው፡፡ ቅድስት ናት ማለታችን የቅድስናዋ ምንጭ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው፡፡ ኵላዊት ናት ማለታችን በክርስቶስ አምኖ የተጠመቀው ሁሉ ሀገር፣ ፆታ፣ ሥራ፣ መልክ ሳይለይ የሚኖርባት ናት ማለታችን ነው፡፡ ሐዋርያዊት ናት ማለታችን ሐዋርያት ከክርስቶስ ተቀብለው ያስተማሯት ናት ማለታችን ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በሐመረ ኖኅ፣ በቤቴል፣ በደብረ ሲና፣ በደብተራ ኦሪት፣ በመቅደሰ ሰሎሞንና በመሳሰሉት ትመሰላለች፡፡

## የቤተክርስቲያን ታሪክ

የቤተክርስቲያን ታሪክ ስንል ቤተክርስቲያን ያከናወነችውንና ሠርታቸው ያለፈችውን፣ በዘመናት ሁሉ የሆነችውንና የሆነባትን ማናቸውንም ነገር የሚነግር ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ታሪክ ምንጮች፦

- መጽሐፍ ቅዱስ
- አዋልድ መጻሕፍት
- በየጊዜው የተደረጉ የቤተክርስቲያን ጉባኤያት
- የቤተክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው መጻሕፍት
- የክርስቲያን መቃብራት፣ መቅደሶች፣ ሥዕሎችና የአርኬዎሎጂ ግኝቶች

የቤተክርስቲያን ታሪክ የክርስትና ሃይማኖት ታሪክ ነው፡፡ በመሆኑም በዋናነት የሰው ልጅ ከአምላኩ ጋር ለዘመናት የነበረውን ግንኙነት ማዕከል ያደረገ የመንፈሳዊ ትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ቤተክርስቲያንን በሚገባ እንድናውቃት፣ ታላቅ ፍቅርና መንፈሳዊ ቅንዐት እንዲኖረን፣ የአኔነት ስሜትን እንድናዳብር ይረዳናል፡፡

## ቤተክርስቲያን በዓለመ መላእክት

አይሁዳዊነት፣ ደቀመዛሙርት፣ ክርስቲያን፣ ኦርቶዶክስ፣ ተዋሕዶ የሚሉት ስሞች በየዘመኑ ለነበረው የእግዚአብሔር አምልኮ መጠሪያ ስሞች ናቸው፡፡ ቅዱሳን መላእክት ደግሞ ከተፈጠሩበት ቀን ጀምሮ ያለ አምልኮተ እግዚአብሔር የኖሩበት ዘመን ስለሌለ ክርስቲያን፣ ኦርቶዶክስ፣ ተዋሕዶ እየተባሉ ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ በዓለመ መላእክት አምላክ ሳይሆን አምላክ ነኝ በማለቱ ሑከት ፈጥሮ የነበረው ሳጥናኤል ነው፡፡ ነገር ግን ቅዱስ ገብርኤል ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ በማለት መላእክትን አረጋግቷቸዋል፡፡ ቅዱሳን መላእክትም በእውነት ጸንተው ከዚያ ጀምሮ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይኖራሉ፡፡ ሳጥናኤልም በመካዱ ምክንያት ከነበረበት የክብር ቦታ ወርዶ ስቃይ ወዳለበት ቦታ ተወርውሯል፡፡

## ቤተክርስቲያን በዘመነ አበው

ዘመነ አበው የሚባለው ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበረው ዘመን ነው፡፡ በዘመነ አበው የነበሩ ሰዎች ይመሩበት የነበረው ሕግ ሕገ ልቡና ይባላል፡፡ ለአዳም ከተሰጡት ሀብታት አንዱ ሀብተ አሚን ነው፡፡ ስለሆነም አዳም በተሰጠው ሀብተ አምልኮ መሠረት በገነት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ለሰባት ዓመት ከሁለት ወር ከዐሥራ ሰባት ቀን ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን ቀድሞ በዓለመ መላእክት ሑከት ፈጥሮ የነበረው ሳጥናኤል አዳምን በማታለል ከአምላኩ ጋር እንዲጣላ አድርጎ ከገነት እንዲባረርና ልጅነቱን እንዲያጣ አድርጎታል፡፡ አዳምም በተሰጠው ሀብተ ክህነት መሥዋዕትን ሠውቶ የመዳን ተስፋን ከእግዚአብሔር አግኝቷል፡፡ አዳም ከገነት ከወጣ በኋላ በደብር ቅዱስ የጸሎት ቦታ ለይቶ ይጸልይ ነበር፡፡ የአዳም ልጆች አቤልና ቃየል በሚስት ምክንያት መሥዋዕት ሠውተው ሳለ እግዚአብሔር በንጹሕ የቀረበውን የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ፡፡ ቃየል ግን በራስ ወዳድነቱ ምክንያት ቀንቶ አቤልን ገደለው፡፡ ከዚህ በኋላ የቃየል ዘሮች ከደብር ቅዱስ ተለይተው ለብቻቸው መኖር ጀመሩ፡፡ ከብዙ ዘመን በኋላ በደብር ቅዱስ ይኖሩ የነበሩ የሴት ዘሮችና በምድረ ፋይድ ይኖሩ የነበሩ ደቂቀ ቃየል በዝሙት አንድ በመሆናቸው ማየ አይኅ በምድር ላይ መጣ፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ ጠፍቶ ኖኅ፣ ካም፣ ሴም፣ ያፌትና ሚስቶቻቸው ብቻ ስምንቱ ተረፉ፡፡ እነዚህ ሦስቱ የኖኅ ልጆችም ምድርን በመልአክ አማካኝነት ለሦስት ተካፍለው በየራሳቸው መንግሥት መሥርተው መኖር ጀመሩ፡፡ ሰውም እየበዛ ትውልዱም ሀገር እየመሠረተ አሁን ያሉ ሀገሮች ሁሉ ለመመሥረት በቅተዋል፡፡ ከሴም ዘር ይወለዱ የነበሩ ሰዎች በብኑ አማካኝነት ጣዖት ማምለክ ጀምረው ከእግዚአብሔር አምልኮ ወጥተው መኖር ጀመሩ፡፡ እንደገና እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ ትክክለኛውን አምልኮ ነግሮታል፡፡ ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ የአማኞች የማመናቸው ምልክት ግዝረት ሆኖ ኖሯል፡፡ ይህ ግዝረት ከሙሴም በኋላ እስከ ክርስቶስ መምጣት የአማኞች ምልክት ሆኖ ኖሯል፡፡

## ቤተክርስቲያን በሕገ ኦሪት

ሕገ ኦሪት የሚባለው ከሙሴ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ የነበሩ ሰዎች ይመሩበት የነበረው ሕግ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ሦስት ዘመናት አሉ፡፡እነዚህም ዘመነመሳፍንት፣ዘመነ ነገሥትና ዘመነካህናት ናቸው፡፡

## ዘመነ መሳፍንት

ከሙሴ ጀምሮ እስከ ሳሙኤል በተነሡ መሳፍንት እስራኤላውያን ይመሩበት የነበረው ዘመን ነው፡፡ በዚህ ዘመን ጎልተው የሚታወቁ መሳፍንት ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ሶምሶን፣ ጌዴዎን፣ ዮፍታሔ፣ ባርቅና ሌሎችም መሪ እየሆኑ እስራኤልን አስተዳድረዋል፡፡ በዚህ ዘመን እስራኤላውያን አንድ ጊዜ ወደ ጣዖት አንድ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እያሉ በዚህም መከራ እየተፈራረቀባቸው ኖረዋል፡፡

## ዘመነ ነገሥት

ዘመነ ነገሥት የሚባለው ከዳዊት ጀምሮ እስራኤላውያን በበደላቸው ምክንያት ወደ ባቢሎን እስከተማረኩበት ጊዜ ያለው ዘመን ነው፡፡ በዘመነ ነገሥት ሰሎሞን ከነገሠ በኋላ ደብተራ ኦሪት በቤተ መቅደስ ተተክታለች፡፡ ምንም እንኳ የንግሥናው ጀማሪ ሳኦል ቢሆንም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር አምፀው የነገሠ የቁጩ ንጉሥ በመሆኑ ሥርወ መንግሥት ከዳዊት ተጀምሯል፡፡ በዘመነ ነገሥት እስራኤላውያን ለሁለት ተከፍለው ሁለት ሀገር መሥርተው ኖረዋል፡፡ ዐሥሩ ነገድ ሀገሩን እስራኤል ከተማውን ሠማርያ ብሎ ሲኖር ሁለቱ ነገድ ማለትም ነገደ ብንያምና ነገደ ይሁዳ ደግሞ ሀገራቸውን ይሁዳ ከተማቸው ኢየሩሳሌም ብለው ኖረዋል፡፡

## ዘመነ ካህናት

ይህንን ዘመን ከዘመነ ነገሥት ጋር ደርበው የሚቆጥሩ አሉ፡፡ ይህ ዘመን እስራኤላውያን በዘሩባቤል አማካኝነት ከባቢሎን ከተመለሱ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ያለው ዘመን ነው፡፡ ከምርኮ መልስ (ሚጠት) በኋላ እስራኤል አንድ ሀገር ሆነው ቀጥለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ካህናትና ነቢያት ኢየሩሳሌምን መልሰው ለማቋቋም ብዙ ደክመዋል፡፡ ዘመነ ካህናት መባሉም ስለዚህ ነው፡፡ እነ ሐጌ፣ ነሕምያ፣ ዕዝራ፣ ዘካርያስና ሌሎችም ነቢያት በዚህ ዘመን የነበሩ ናቸው፡፡

## በሕገ ኦሪት ምን ነበር?

- ካህናት ይሆኑ የነበሩት ከነገደ ሌዊ የሚወለዱት ብቻ ነበሩ
- ነገሥታት የሚሆኑት ብዙ ጊዜ ከነገደ ይሁዳ የሚወለዱት ነበሩ
- ብዙ የመሥዋዕት አቀራረብና የመሥዋዕት ዓይነቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ነበሩ
- በየዘመኑ ነቢያት ከእግዚአብሔር ተልከው እየመጡ ያስተምሩ ነበር
- ሐሰተኛ ነቢያትና ክፉ ነገሥታት እየተነሡ ሕዝቡን ይበጠብጡ ነበር

በዘመነ ኦሪት መጨረሻ አካባቢ እስራኤላውያን በእምነትም በአመለካከትም ተለያይተው የተለያዩ ቡድኖችን መሥርተው ይኖሩ ነበር፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ፈሪሳውያን፡- ከትንሣኤ በኋላ ማግባት መጋባት አለ ይሉ የነበሩ ናቸው
- ሰዱቃውያን፡- ትንሣኤ ሙታን የለም ብለው የሚያምኑ ናቸው
- ኤሲያውያን፡- የመሚሑን መምጣት በጾም በጸሎት ሆነው በኩምራን ደሴት ይጠብቁ የነበሩ ናቸው፡፡ መሚሐ ሲመጣ ከሮማ ቅኝ ግዛት ነጻ ያወጣናል ብለው ያስቡ ነበር፡፡

## ቤተክርስቲያን በሐዲስ ኪዳን

ከክርስቶስ ጀምሮ ያለው ዘመን ዘመነ ሐዲስ/ ዓመተ ምሕረት ሲባል የምንመራበት ሕግ ደግሞ ሐዲስ ኪዳን ይባላል። የሚጠበቀው መሢሕ ራሱ ክርስቶስ ሆኖ ሳለ ብዙ እስራኤላውያን ግን ምድራዊ ገዥን ጠብቀው ክርስቶስን ሳይቀበሉት ቀርተዋል። የሐዲስ ኪዳን የቤተክርስቲያን ታሪክ በአምስት ይከፈላል። ይኸውም ዘመነ ሥጋዌ፣ ዘመነ ሐዋርያት፣ ዘመነ ሐዋርያውያን አበው፣ ዘመነ ሰማዕታትና ዘመነ ሊቃውንት ናቸው።

## ዘመነ ሥጋዌ

ይህ ዘመን ወልደ እግዚአብሔር ሰው ከሆነበት ከጽንሰቱ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ያለው ዘመን ነው። ክርስቶስ በዚህች ምድር በሥጋ እየተመላለሰ ያስተማረበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመን ክርስቶስ ሕገ ወንጌልን አስተምሯል። ከፅንሰቱ እስከ ዕርገቱ በሠራቸው ሥራዎችም የሰውን ልጅ አድኖታል።

## ዘመነ ሐዋርያት

ሐዋርያ የሚለው ቃል ሖረ-ሄደ ከሚለው የግእዝ ግሥ የሚገኝ ሲሆን የተላከ፣ ሂያጅ፣ ልኡክ ማለት ነው። ሐዋርያት ወንጌልን፣ ድኅነተ ዓለምን ለመላው ዓለም ሊያውጁ ወይም ሊያበስሩ ተልከዋል። ቅዱስ ጳውሎስም ካመነ በኋላ ወንጌልን በስፋት በማስተማሩ ሐዋርያ እየተባለ ይጠራል። ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ግን አይደለም። ዘመነ ሐዋርያት የሚባለው ከ34 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 70 ዓ.ም ያለው ዘመን ነው። በዚህ ዘመን ሐዋርያት ከክርስቶስ የተማሩትን ትምህርት ወደ ዓለም ሁሉ እየዞሩ አስተምረዋል። 12ቱ ሐዋርያት የሚባሉትም፡-

1. ቅዱስ ጴጥሮስ (ኬፋ/ስምዖን)
2. ቅዱስ እንድርያስ
3. ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ (ፍቁረ እግዚእ፣ ታዖሎጎስ፣ አቡቀለምሲስ)
4. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ
5. ቅዱስ ፊልጶስ
6. ቅዱስ በርተሎሜዎስ
7. ቅዱስ ቶማስ (ዲዲሞስ)
8. ቅዱስ ማቴዎስ
9. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ
10. ቅዱስ ታዴዎስ (ልብዴዎስ)
11. ቅዱስ ናትናኤል (ስምዖን ቀነናዊ)
12. ቅዱስ ማትያስ (በዕጣ በይሁዳ ምትክ የተተካው ሐዋርያ)

ናቸው። ጌታ ከሐዋርያት በኋላ የመረጣቸው ሐዋርያትን በስብከት የሚረዱ 72 አርድዕት፣ በገንዘባቸው የሚረዱ ለተልዕኮ የሚፋጠኑ 36 ቅዱሳት አንስት ነበሩ። ከአራቱ ወንጌላውያን ማርቆስና ሉቃስ ከ72ቱ አርድእት መካከል ናቸው። ሐዋርያት ወንጌልን በማስተማራቸው ልዩ ልዩ መከራ ደርሶባቸዋል። በሐዋርያት ዘመን የነበሩት የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ኑሮ የአንድነት ኑሮ ነበር። ምግባቸውም በአንድ ላይ ስለነበረ የፍቅር መዓድ (አጋፔ) ይባል ነበር።

በዘመነ ሐዋርያት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን በገንዘብ ሊገዛ የነበረ ሲሞን ተነሥቷል ነገር ግን ቅዱስ ጴጥሮስ በጸሎቱ አጥፍቶታል፡፡

## በዘመነ ሐዋርያት የክርስትና መስፋፋት ምክንያቶች

- ብሉይ ኪዳን ቀድሞ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ መተርጎሙ
- የሐዋርያት ስብከት
- የሮም ግዛት ሰፊ ስለነበረ ያለ ይለፍ ወረቀት ከአንዱ ሀገር ወደ አንዱ ሀገር መሄድ መቻሉ ለሐዋርያት ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ
- የክርስቲያኖች ፍቅር ሌሎችን ይስብ ስለነበር
- ክርስቲያኖች በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ወደ ዓለም መበተናቸውና በየሄዱበት ሀገር ማስተማራቸው

## ዘመነ ሐዋርያውያን አበው

ዘመነ ሐዋርያውያን አበው የሚባለው ከ70 ዓ.ም እስከ 160 ዓ.ም የነበረው ዘመን ነው፡፡ ሐዋርያውያን አበው የሚባሉት ከሐዋርያት ተምረው በሐዋርያት መንበር ተተክተው ያስተማሩ አባቶች ሲሆኑ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ
2) ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም ረድአ ጴጥሮስ
3) ቅዱስ ሄሬኔዎስ ዘሀገረ ኤዶም
4) ቅዱስ ፖሊካርፕስ

በዘመነ ሐዋርያትና ሐዋርያውያን አበው ዘመን ከነበሩ የውስጥና የውጭ ጠላቶች መካከል ቢጽ ሐሳውያንና ግኖስቲኮች ይጠቀሳሉ፡፡ በሐዋርያት ዘመን የግሪኮች የፍልስፍና ትምህርትና አስተሳሰብ በአብዛኛው የምዕራቡ ዓለም እንደ እምነት ይታይ ስለነበር አንዳንድ የፍልስፍና እይታዎች ፀረ ወንጌል ሆነው ያስቸግሩ ስለነበር ለእነዚህ ምላሽ ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሯል፡፡

- ቢጽ ሐሳውያን፡- እነዚህ ሐሰተኛ ወንድሞች ሲሆኑ ጥምቀት ያለ ግዝረት፣ ወንጌል ያለ ኦሪት አይጠቅምም እያሉ ያስተምሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው
- ግኖስቲኮች፡- እነዚህ ደግሞ መዳን በዕውቀት ብቻ እንጂ በእምነት አይደለም ይሉ የነበሩ ናቸው፡፡ በዘመናቸው የነበረውን የፍልስፍና፣ የጥንቆላና የምትሐት እንዲሁም ልማዳዊ አስተሳሰቦችን ከክርስትና ትምህርት ጋር ይቀላቅሉ ነበር፡፡ ክርስትናን ከእምነት ይልቅ በፍልስፍና ላይ ለመመሥረት ይጥሩ ነበር፡፡ ክፉ አምላክና ደግ አምላክ የሚባሉ አማልክት አሉ ይሉ ነበር፡፡

## ዘመነ ሰማዕታት

ዘመነ ሰማዕታት የሚባለው ከ160 ዓ.ም እስከ 312 ዓ.ም የነበረው ዘመን ነው፡፡ ይህ ዘመን ክርስቲያኖች በአዋጅ መከራ እንዲደርስባቸው የተደረገበት ነው፡፡ ሰማዕታት ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ የነበሩ ቢሆንም በመከራው ጽናት የተነሣ በተለየ ዘመነ ሰማዕታት የሚባለው ዘመን ይህ ነው፡፡ የሐዋርያትንም ታሪክ ስንመለከት የብዙዎቹ በሰማዕትነት ያሸበረቀ ሕይወት ነው፡፡ ኔሮን ቄሣር (57 ዓ.ም- 68 ዓ.ም) የሮም ከተማን ራሱ አቃጥሎ ክርስቲያኖች አቃጠሉት በማለት

በክርስቲያኖች ላይ መከራ እንዲደርስ አድርጓል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና ሐዋርያው ጳውሎስ ሰማዕትነታቸውን የፈጸሙት በዚህ ዘመን ነው፡፡ የሮማ መኳንንት በሮም ግዛት ረኀብ፣ ቸነፈር፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የመሳሰሉት ችግሮች በደረሱ ቁጥር በክርስቲያኖች ምክንያት የሮም አማልክት ተቆጥተው ያወረዱብን ቅጣት ነው እያሉ በክርስቲያኖች መከራ ያደርሱ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ምንም ወንጀል ሳይሠሩ ለተራቡ አንበሶች ይጣሉ ነበር፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ወደ ፍጥሞ ደሴት የተጋዘ በድምጥያኖስ ዘመነ መንግሥት (81 ዓ.ም- 96 ዓ.ም) ነበር፡፡ የተጋዘበት ምክንያትም ድምጥያኖስ የራሱን ምስል አሠርቶ እንዲሰገድለት ስላዘዘና ዮሐንስ ደግሞ ይህንን በመቃወሙ ነበር፡፡ ቅዱስ አግናጥዮስ የሰማዕትነት ተጋድሎውን የፈጸመው በትራጃን ዘመነ መንግሥት (98 ዓ.ም- 117 ዓ.ም) ነው፡፡ ትራጃን በኀይል ብቻ ሳይሆን በዘዴና በማስፈራራትም ጭምር ክርስቲያኖችን ወደ ቤተ ጣዖት ለመመለስ ይጥር ነበር፡፡ በዓይነቱም ሆነ በብዛቱ ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው የክርስቲያኖች እልቂት የተፈጸመው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት (284 ዓ.ም-305 ዓ.ም) ነው፡፡ የዲዮቅልጥያኖስ አዋጅ በቤተክርስቲያን ላይ የሚከተለው ነበር፡፡

- አብያተ ክርስቲያን ተቃጥለው አብያተ ጣዖታት እንዲከፈቱ
- የቤተክርስቲያ ንብረት ሁሉ እንዲወረስ
- ማንኛውም የሮማ ዜጋ ክርስቲያን ከሆነ ከመንግሥት ሥራ እንዲባረር
- ባሮች ክርስትናን ከተቀበሉ ነጻ የመውጣት መብት እንደሌላቸው
- ክርስቲያኖች ምንም ሕጋዊ ምክንያት ቢኖራቸው በማንም ላይ ክሥ መመሥረትና ስለ መብታቸው መከራከር አይችሉም የሚል ነበር

ከዚህ በኋላ ለጣዖት መሥዋዕት አናቀርብም ያሉ ሰዎችን ከአራዊት ጋር በማታገል፣ በመጋዝ በመሰንጠቅ፣ በእሳት በማቃጠል፣ ለተራቡ አውሬዎች በመጣልና በልዩ ልዩ መከራዎች አሰቃዩዋቸው፡፡ እንደዚህ ያሉት ስቃዮችም ክርስቲያኖችን በማጥፋት ፈንታ እያደፋፈሯቸውና እያበረቷቸው ይሄዱ ነበር፡፡ ዲዮቅልጥያኖስ ከሞተ በኋላ ቆስጠንጢኖስ ነገሠ፡፡ ቆስጠንጢኖስ ከእናቱ ከእሌኒና ከአባቱ ከቁንስጣ ተወለደ፡፡ ለቆስጠንጢኖስ በጠፈረ ሰማይ "በዚህ የመስቀል ምልክት ድል ታደርጋለህ/በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ፀረከ/ኒቀስጣኑ ኒቀስጣጣኑ" የሚል ተጽፎ አይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በፈረሱ አንገትና በመሣሪያው ጫፍ የመስቀል ምልክት አስደርጎ፣ ጠላቶቹን ገጥሞ አሸነፋቸውና ነገሠ፡፡ ለቤተክርስቲያንም የሚከተሉትን መብቶች ሰጠ፡፡

- ✓ ቤተ ክርስቲያን ከግብር ነጻ እንድትሆን
- ✓ ዕለተ እሑድ ሥራ እንዳይሠራባት
- ✓ በክርስቲያኖች መካከል የሚፈጠሩ አንዳንድ አለመግባባቶች ቢኖሩ ለኤጲስ ቆጶሱ የዳኝነት ሥልጣን ተሰጥቷል

## ሁለቱ የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች

በቤተክርስቲያን ታሪክ የሚታወቀው የመጀመሪያው የክርስቲያኖች ትምህርት ቤት በ60 ዓ.ም በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ የተመሠረተው የእስክንድርያ የትርጓሜ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የትምህርት ቤቱም ዓላማ አማኞችን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ለማሰልጠንና ከዚያም ሲወጡ ወገኖቻቸውን ለማስተማር የሚያስችለውን መንፈሳዊ ዕውቀት እንዲገበዩበት ነው፡፡ ሁለተኛው ትምህርት ቤት በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሉቅያኖስ አማካኝነት የተመሠረተው

የአንጾኪያ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የሁለቱም ትምህርት ቤቶች መመሥረት በክርስትና ብዙ ሊቃውንትንና ጳጳሳትን አስገኝቷል፡፡ የእስክንድርያ ትምህርት ቤት ምሥጢራዊ ትርጓሜ (Allegorical interpretation) ላይ ያተኮረ የትምህርት አሰጣጥን ሲከተል የአንጾኪያው ትምህርት ቤት ደግሞ ነጠላ ትርጓሜ (literal interpretation) ላይ ያተኮረ ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡

## ዘመነ ሊቃውንት

ከጉባኤ ኒቅያ ጀምሮ ያለው ዘመን ዘመነ ሊቃውንት ይባላል፡፡ በዘመነ ሊቃውንት የተደረጉ ሦስቱ ዐበይት ዓለማቀፍ የቤተክርስቲያን ጉባኤያት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ጉባኤ ኒቅያ፡- በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በ325 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን ከሓዲው አርዮስ፣ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ብዛት 318፣ የጉባኤው አፈ ጉባኤ እለ እስክንድሮስ ነው፡፡
- ጉባኤ ቍስጥንጥንያ፡- በታላቁ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት በ381 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን ከሓዲው መቅዶንዮስ፣ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ብዛት 150፣ የጉባኤው አፈ ጉባኤ ጢሞቴዎስ ዘአልቦ ጥሪትና ለተወሰነ ጊዜ ደግሞ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ነበር፡፡
- ጉባኤ ኤፌሶን፡- በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት በ431 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን ከሓዲው ንስጥሮስ፣ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ብዛት 200፣ የጉባኤው አፈ ጉባኤ መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ ነበር፡፡

በሁሉም ጉባኤያት በየዘመናቸው የተነሡ የተሳሳቱ ትምህርቶችን እያወገዙ ትክክለኛውን የቤተክርስቲያን አስተምህሮ እየገለጹ ኖረዋል፡፡ ጉባኤ ኬልቄዶንን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አትቀበለውም፡፡ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተመሠረተች በጉባኤ ኬልቄዶን ነው፡፡ የጉባኤ ኬልቄዶን ተሳታፊዎች መለካውያን ይባላሉ፡፡ መለካውያን ማለትም የእግዚአብሔርን ሳይሆን የንጉሥን ፈቃድ የሚፈጽሙ ፈጻምያነ ፈቃደ ንጉሥ ማለት ነው፡፡ የኬልቄዶን ጉባኤ ጉባኤ ከለባት (የውሾች ጉባኤም) እየተባለ ይጠራል፡፡ የምሥራቅ ኦርቶዶክሶች በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (1054 ዓ.ም) ከካቶሊክ የተለዩ ናቸው፡፡ አኀት አብያተ ክርስቲያን (Oriental Orthodox Churches) የሚባሉት የኢትዮጵያ፣ የአንጾኪያ (ሶርያ)፣ የእስክንድርያ (ግብጽ)፣ የሕንድ፣ የአርመንና የኤርትራ አብያተ ክርስቲያን ናቸው፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተለይቶ የመጣ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪት፣ በሕገ ወንጌል እግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረችና እያመለከች ያለች ሀገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና እግዚአብሔርን ታመልክ እንደነበረ ማሳያው ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን የተናገረችው ንግግር ነው፡፡ “አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን” ይላል (1ኛ ነገ.10፥9)፡፡ ንግሥተ ሳባ ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን ወልዳለች፡፡ በቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮንና በጠቅላላው ሕገ ኦሪት ወደ ሀገራችን መጥቷል፡፡ ከዚያ ጀምሮም ኢትዮጵያ በሕገ ኦሪት ስትመራ ቆይታለች፡፡ ለዚህም ማስረጃው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው (የሐዋ. ሥራ 8፥27-39)፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከፊልጶስ ከተጠመቀ በኋላ ወደ ሀገሩ መጥቶ ክርስትናን እንዳስተማረ ይታመናል፡፡ ከዚያ በኋላ ፍሬምናጦስ (አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን) ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ከቅዱስ አትናቴዎስ ኤጲስ ቆጶስነትን ተሹሞ በሀገራችን ክርስትናን አስፋፍቷል፡፡ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግእዝ

ቋንቋ እንዲመለሱ አድርጓል፡፡ ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን አድርጓል፡፡ ነገሥታቱ አብርሀ ወአጽብሐ (ኢዛናና ሳይዛና) አብያተ ክርስቲያንን በማሳነጽ ታላቅ አበርክቶ አበርክተዋል፡፡ ከዚያ በኂላ ከሮምና ከሌሎች ሀገሮች ተሰደው የመጡ ተስዓቱ ቅዱሳን ገዳማትን በመመሥረትና ክርስትናን በማስተማር ታላቅ ውለታ ውለውልናል፡፡ ተስዓቱ ቅዱሳንe የሚባሉትም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አባ ገሪማ (ይስሐቅ)
- አባ አረጋዊ (ዘሚካኤል)
- አባ ጰንጠሌዎን
- አባ አፍጼ
- አባ ጉባ
- አባ አሌፍ
- አባ ሊቃኖስ
- አባ ይምዓታ
- አባ ጽሕማ

ናቸው፡፡ ከእነርሱ ቀጥሎ ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያን በማሕሌት እንድታሸበርቅ አድርጓል፡፡ ነገሥታቱ እነ አጼ ካሌብ፣ አጼ ገብረ መስቀል፣ የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ነገሥታት (ቅዱስ ላሊበላ፣ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ነአኵቶ ለአብ፣ ቅዱስ ሐርቤ/ገብረ ማርያም) አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽና ክርስትናን በማስፋፋት ታላቅ ውለታን ውለውልናል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዮዲት ጉዲት እና በግራኝ ምክንያት ብዙ ጥፋት ደርሶባታል፡፡ በየመካከሉም ታላላቅ ሊቃውንት ተነሥተው አስተምረዋል፡፡ ምሳሌ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይጠቀሳል፡፡ ቅዱሳኑ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡